# ልኬ

(ፉአድ ሙና)

.

የቢሮዉ ጠረጴዛ ላይ ግማሹ የተጠጣ ማኪያቶ በትንሽዬ ብርጭቆ ተቀምጧል። ጥቁሩ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሀሰን ተቀምጦ አንድ ያረጀ መፅሀፍ ያነባል። ወንበሩ አልተመቸዉም። እጆቹን የወንበሩ እግር ስር እየላከ ወንበሩን ከፍ ……ዝቅ…… ለጠጥ……… ቀና ያደርገዋል። ወንበሩ ጀማሪ ሰራተኛን ለማስቀመጥ ማኩረፉ ንቀት አሊያም የሀሰን ከሲታነት ላይ የሚያላግጥ አስመስሎበታል። መፅሀፏን ገፆቿ መካከል ለምልክት የምትሆን ነጭ ወረቀት አኑሮባት ከደናትና ጠረጴዛዉ ላይ አስቀመጣት። ከአጠገቡ ወዳለዉ ኮምፒዩተር ዞሮ ትንሽ ነካካና አጨለመዉ። ስልኩን አብርቶ ሰዓቱን ተመለከተና አልላመድህ ካለዉ ወንበር ላይ እየተንጠራራ ተነሳ። እዚህ መስሪያ ቤት ከተቀጠረ ሶስት ወር ሞልቶታል። ፊቱ ከፂም የፀዳች ስለሆነች በጣም ልጅ ይመስላል። ስራዉን ጨርሶ ትንሽ ዕረፍት ሲያገኝ ማንበብ ይወዳል።

ከወንበሩ ከተነሳ በኋላ የቢሮው ጥግ ላይ ወዳለዉ ልብስ መስቀያ ሶስት እርምጃ ተራምዶ ደረሰና ጥቁር የሱፍ ኮቱን ደረበ። አይኑን ወደ ታች ቀብሮ አለባበሱን ቃኘ። ከስር የለበሰዉ ዳለቻ የጨርቅ ሱሪ ከወደ እግሩ አካባቢ ሰዉነቱ ላይ ሰብሰብ ብሎ ወጣትነቱን ይመሰክራል። ገና ያልበረደ የአፍላነት እሳት ……. ስለራስ የመጨነቅ ያልተዳከመ ሀይል ይታይበታል።

ከጠረጴዛዉ ላይ መፅሀፉን አንስቶ ሙሉ ዙሪያዉን እኩል የተቆረጠ እንደ ኑግ የጠቆረ ፀጉሩን ዳበሰ። የግራ እጁ ወደ ኪሱ ተመልሶ ቁልፍ ይዞ ወጣ። የቢሮዉን መብራት አጥፍቶ አሮጌዉን መፅሀፍ የቀኝ ብብቱ ዉስጥ ይዞ ቢሮውን መቆለፍ ጀመረ።

በሽያጭ መስሪያ ቤቱ ዉስጥ መንገድ ላይ ያጋጠሙትን ሰራተኞች ሰላም እያለ ሁለት ፎቅ ወርዶ ከመስሪያ ቤቱ ወጣ።

.

ሜክሲኮ ልዩ የህዝብ በዓል እንደሚከበርባት ሁሉ በሰዉ ብዛት ተጨናንቃለች። ከስራ የሚመለሰው ህዝብ በፍጥነት በአንድ አቅጣጫ ይተማል። ታክሲ እና አዉቶብሶችን ተሰልፎ የሚጠብቀው ህዝብ በሚደንቅ ትዕግስት መጨረሻዉ በአይን የማይዘለቀውን ሰልፍ ተያይዞታል። ሰልባጅ ልብሶችን አንጥፈው የሚሸጡ ፣ እድሜ የሌላቸዉ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶችን አንገታቸዉና ትከሻቸው ላይ ያንጠለጠሉ ……. ሌሎችም ብዙ የመንገድ ዳር ነጋዴዎች መንገዱን ሞልተውታል።

ሀሰን አሮጌዋን መፅሀፍ እያወዛወዘና ጥቁሯን አንፀባራቂ ጫማዉን እያየ በመንገዱ ላይ ይራመዳል። "ወጥመዷን በአስር ብር! ሰላምዎን በአስር ብር!" የሚል ወጥመድ ሻጭ ወጥመዱን አይኑ ላይ ሲያወዛዉዝበት ጫማዉ ላይ ተዓምር እየፈለጉ የነበሩ አይኖቹን ነቅሎ ተመለከተዉና መንገዱን ቀጠለ። የእግረኛዉ ብዛት ……. ትርምሱ ……. ጩኸቱ ስልችት ብሎታል። አይኑን ወደ ጫማው መልሶ መራመዱን እንደቀጠለ ከጀርባዉ ሸቀጣቸዉን ተሸክመው የሚሮጡ ነጋዴዎች እየገፈታተሩት አለፉ። ቀና ሲል ከፊቱ ያሉትም የመንገድ ዳር ነጋዴዎች ሸቀጣቸውን ተሸክመዉ ይፈረጥጣሉ። ወደ ኋላ ዞር ብሎ ሲመለከት ከስር ጎመን የሚመስል አረንጓዴ ሱሪ ከላይ ደግሞ ዳለቻ ቀለም ያለዉ ሸሚዝ የለበሱና

ጎናቸዉ ጋር ቡኒ የቆዳ ቦርሳ ያሰሩ ደንቦች ጥቁሯን ዱላቸዉን እያወነጨፉ ነጋዴዎቹን ሲያባርሩ ተመለከተ። ፈገግ አለ። ሁሌም ስለደንቦች ሲያስብ ጠባብ አይኖቹ የተጨፈኑ እስኪመስሉ ድረስ ፈገግ ይላል። ስራ የመከልከል ስራ የተሰጣቸዉ ስራ ከልካይ ሰራተኞች መሆናቸዉን ያስብና እንደ እብድ ይስቃል። የመንገዱ መካከል ላይ የቆመው የባቡር ሀዲድ ተሸካሚ ድልድይ የመጨቆን ድምፅ አሰማ። ባቡር እያለፈበት ነበር። ቀና ብሎ ባቡሩን ተመለከተና በማደያዉ በኩል ወደ አደባባዩ መጓዙን ቀጠለ። የእግረኛ መንገዱ ላይ ማዳበሪያ አንጥፎ ተጠቅልሎ የተኛ ልጅ ተመለከተ። ከአጠገቡ ባለው ድምፅ ማጉያ (ሜጋ ፎን) አንጀት የሚበላ የዋሽንት ድምፅ ይንቆረቆራል። ልመና በጥበብ ታጅቦ ቀርቧል። ሀሰን ብዙ ጊዜ እነዚህን ለማኞች እና የሀገራችንን የሬዲዮ ጣቢያዎች ያነፃፅራቸዋል። ድምፅ አጠቃቀም ለማኞቹ ሳይበልጡ አይቀሩም ብሎ ያስባል።

እየተራመደ አንገቱን ቀና ባደረገ ቁጥር አይኑ መንገዱ ላይ ከሚርመሰመሱት እንቡጥ የተራቆቱ ገላዎች ጋር እየተጋጨች ልቡን ታስጨንቅበታለች። ስራ ባያስገድደው ሜክሲኮን ዞር ብሎ ባያየት ይመርጣል። ትንሽ እንደተራመደ ያደረገችው ባለተረከዝ ጫማ ያደናቀፋት ቆንጆዬ እንስት እግሩ ላይ ወደቀች። እጆቿ የሱሪውን ቀኝ እግር ስለጎተቱት ሱሪው ዝቅ አለ። ዞር ብሎ ሲመለከታት እየተስለመለመች "ይቅርታ ...." አለችዉ። ከላይ የለበሰችው ወንፊት መሳይ ሹራብ ሙሉ ሰዉነቷን ያሳያል። ብርቱካናማ የጡት ማስያዣ አድርጋለች። ቀሚሷ ፍም የመሰሉ ጭኖቿን ያስጎበኛል። በጭኑ መካከል ቁራጭ ስጋው ተንፈራገጠች ........ ልቡ ጨዋነቷን እንደተገፈፈች አስቦ ተጨነቀ።

ልጅቷ ተነስታ እያነከሰች ....... ህመሟን ላለማሳየትም ፈገግ እያለች ሄደች። የእግረኛ ማቋረጫው ጋር ሲደርስ በማትችለዉ እንግሊዘኛ ገብታ እንግሊዘኛዉን በሀገርኛ ዘዬ የምትፈጨው ሴትዮ "ዚስ ኢዝ ዘ ቤድስትሪያል ሬድ ላይት ብሊስ ዶንት ባስ" ስትል ሰምቷት እንደተለመደው እየሳቀ ታክሲ ወደ ሚይዝበት የአረቄ ፋብሪካው አጥር ሄደ። ለምን እንደሚስቅ እሱም አያውቀውም። በቃ ያስቀዋል።

.

ወደ ታክሲው ሰልፍ ሲደርስ ሁለት መጨረሻቸው የማይታይ ረዣዥም ሰልፎችን ተመለከተ። በግራ በኩል ያለውን ሰልፍ ተከትሎ መጨረሻውን ለማግኘት ረዥም ርቀት ተጓዘ። የሰልፉ መሀል ላይ አንዲት ሴት ፈገግ ብላ ሰልፉ መሀል እንዲገባ ጋበዘችው። ፈገግ አለላት። የጓደኛው ወዳጅ ናት። ሊያገባት ብሎ ቁመቷ ብቻ ያሰረዉ! አጭር ሴት አይወድም። የሀሰን ጓደኛ! ፈገግ እንዳለ የአመልካች ጣቱን በአሉታ አወዛውዞ ወደ ሰልፉ መጨረሻ ሄደ።

ሀቀኝነት ከራስ እንደሚጀምር ያምናል። ሰልፍ አጭበርብሮ ታክሲ የሚሳፈር ሰው ነገ ስልጣን ቢሰጠው የህዝብ ሀብት የማያጭበረብርበት ምክንያት አይታየውም። ሰልፍ መሀል ቆመው ወዳጃቸውን ወደ ሰልፍ ጠርተው የሚያስገቡ ሰዎች ሌላዉ የመንግስት ሀላፊ በዘመድ ሰራተኛ መቅጠሩን ሲያወግዙ ያስቀዋል። ሀቀኝነት በስልጣኑ መጨመርና መቀነስ አይለካም። ከዚህ የተጀመረች ንቅዝና ናት በስልጣን ስትፈረጥም ህዝብን ደም የምታስነባዉ ይላል።

የሰልፉ መጨረሻ ላይ ሲደርስ ለማረጋገጥ ያህል ከፊቱ የቆመችውን ልጅ "የጦርሀይሎች ሰልፍ ነው አይደል?" ብሎ ጠየቃት። ልጅቷ በአዎንታ አንገቷን ነቀነቀችለት። ቀኑ ወደ መጨለሙ ተጠግቷል። መፅሀፉን ከፍቶ ማንበብ ጀመረ። በንባቡ ተመስጦ ሰልፉ ወደ ፊት በተጠጋ ቁጥር አይኑን ከመፅሀፉ ላይ ሳይነቅል በደመነፍስ ይራመዳል። ሰልፉ ረዥም ስለነበር እንደተሰለፉ ጨለመ። የመንገድ መብራቱ

በቂ ብርሀን ስለነበረው ከንባቡ አልተገታም። አንድ ፈርጠም ያለ ክንድ በትከሻው በኩል አልፎ የሚያነበውን መፅሀፍ አጠፈው። ማንነቱን ለማየት ሲዞር ትከሻው አካባቢ የመጠጥ ሽታ በስሱ ሸተተዉ። ቀድሞ ቀመሱ እጅብ ያለ ፀጉሩ የጎፈረ ጎልምሳ "አሪፍ መፅሀፍ ነዉ።" አለና መፅሐፉን ለቀቀለት። ፈገግ አለና ፊቱን ወደ መፅሀፉ አዙሮ ፈገግታውን ክስም አደረገው። የውሸት ፈገግታ ነበር …….. ንዴትን ለመሸፈን የተሰራ!

.

ሀሰን መፅሀፉ ላይ ተመስጧል። ሰዉ ግን ይተረማመሳል። ከጎኑ ያለው ሌላኛው ሰልፍ ላይ ያለሰልፋቸው በድፍረት ከፊት የሚቆሙ ሰዎችን እንዲያባርርላቸው ሰልፈኞች ተራ አስከባሪዎች ላይ ይጮኻሉ። አንድ ያለሰልፉ የቆመ አመድ የመሰለ ልጅ ተራ አስከባሪውን "አስወጣው!" የሚሉት ተሰላፊዎች ላይ አይኑን አጉረጠረጠ። ከተሰላፊዎቹ አንዷ "እዩው ሊሳደብ ነዉ አጉረጠረጠ! እዩው ሲነፋፋ!" አለች። ልክ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ጣልቃ ገቦች እንደሰደቧት ሁሉ። ስድባቸው ምንድነው? ተራ ስድብ? አይደለም። ያጋለጣቸውን ሰው አፍ ለማዘጋት የሚጠቀሙት ቆንጆ የስነ ልቦና ጥበብ ነው። አጭበርብሮ በድፍረት መሳደብ! …….. ያጋለጣቸው ሰው ሀጢያተኛ እንደሆነ ሁሉ!

.

ሀሰን ከመፅሀፉ ድርሰት ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪዎች በአእምሮው እየሳለ ከሚያውቃቸው ሰዎች ጋር ያመሳስላል። ከኋላው አንድ የሴት ድምፅ "ይኼ የአየር ጤና ሰልፍ ነው አይደል?" ሲል ተሰማው። አይኖቹን ከመፅሀፉ ላይ ነቅሎ ዞር ብሎ ተመለከታት። ቀይ ናት! ባለሰልካካ አፍንጫ! ከንፈሯ በስሱ ቀይ ሊፒስቲክ የተቀባ! የተሰለፈችው ከእርሱ ኋላ ነበር። ከእርሷ ኋላ ደግሞ መፅሀፉን ያጠፈበት ፣ በመጠኑ የቀማመሰ ጨበሬ ጎረምሳ ቆሟል። በመሀከላቸው የነበረችውን ልጅ አልፎ መጥቶ መፅሀፉን እንዳጠፈበት ገባውና ተገረመ።

"አዎ! አየር ጤና፣ ዘነብወርቅ ምናምን ነው!" አላትና አይኖቹን ወደ መፅሀፉ መለሰ።

ከልጅቷ ኋላ የቆመው ጎረምሳ የቀበቶ መታጠቂያው ዙሪያውን ተማሪዎች ለፈተና ሲሄዱ የሚያስሯትን ትንሽዬ ቦርሳ አስሯል። ከፊቱ ያለችውን ሴት አናገራት።

"አምሮብሻል! የእውነት! ፐ ……. ውበት!"

ልጅቷ ነገረ ስራው መሯታል መሰል በዝምታ አለፈችው። ውስጧ ላይ የመረበሽ ስሜት ይንጣታል። ደህንነት አይሰማትም። ባለ ጨበሬው ትከሻዋን ነካ አደረገና ሀሰን ወደሚያነበው መፅሀፍ እየጠቆመ "በጣም ምርጥ መፅሀፍ ነው። ይገርምሻል አንብቤዋለሁ!" አለና እጆቹን ወደ መፅሀፉ ልኮ ድጋሚ ሽፋኑን አጥፎ ተመለከተው። እጆቹ ወደ ፊት ሲንጠራሩ አካሉ የልጅቷ ጀርባ ላይ ተለጠፈ። ዙሪያውን ያሰረው ቦርሳ የልጅቷ ቀሚስ ላይ ተለጥፎ እየተንቀሳቀሰ መቀመጫዋን ይነካካታል። ጉንጮቿ ቀሉ። አይኖቿ ፍርሀቷን በግልፅ ያስነብባሉ። ጎረምሳው መፅሀፉን ለቆ ወደ ቦታው ሲመለስ ቦርሳው ከመቀመጫዋ ተላቀቀ። ሀሰን ለጎረምሳው ትኩረት ሳይሰጥ ንባቡ ላይ ተመስጧል። ጎረምሳው በስልት ቦርሳውን ወደ ልጅቷ መቀመጫ አስጠግቶ ያነቃንቀዋል። ከልጅቷ አይኖች እንባ ሞልቶ ሊፈስ አኮበኮበ። ተው እንዳትለው በጣም ግዙፍ ነው። መላ አካሏ በፍርሀት ተሸብቦ ወደ ሀሰን ተጠጋችና "ይቅር ታ ከጎንህ መቆም እችላለሁ?" አለችው። ፈገግ ብሎ "ይቻላል!" አላትና ወደ ንባቡ ተመለሰ።

አሁን ሀሰን ከኋላ ያለው ጎልማሳ ጨበሬ ልጅቷን እያስቸገራት እንደሆነ ስለገባው ትኩረቱን መፅሀፉ ላይ ያደረገ አስመስሎ የጎረምሳውን ድርጊት መከታተል ጀምሯል።
ጎረምሳው "ኧረ ትዕግስት ይግባሽ!" አለና በረዥሙ እየተነፈሰ ........ ልክ አግብቷት አትንካኝ እንዳለችው ሁሉ ......... በእርሷ ትክክል ወደ ጎን ወጥቶ ቦርሳውን መቀመጫዋ ላይ ማሸቱን ቀጠለ። ሀሰን ባየው ነገር በጣም ተማረረ። መማረር መፍትሔ ባይሆንም ተማረረ። ልጁን ግደለው ግደለው አለው። የመግደል አቅም ያለው ይመስል ......... ድሮም ትግል አይወድም። ዛሬ ግን ጉልበት ኖሮት ልጅቷን ነፃ ሊያወጣት ተመኘ። ልቡ እርብሽብሽ ብሏል። አይኖቹ መፅሀፉ ላይ ይረፉ እንጂ ፊደል ይሁን ቁጥር የሚያየው አያውቅም። የልጅቷ ከንፈሮች በፍርሀት ይንቀጠቀጣሉ። ሳግ ባነቀው ድምጿ "ከፊትህ ልሁን?" አለች መፅሐፉ ላይ በትካዜ ያፈጠጠውን ሀሰንን አይኖች በአይኖቿ እየተለማመጠች። ከልቡ የነበረው ሀዘን ፣ ምንም ማድረግ ያለመቻል ቁጭት ብስጭት ብስጭትጭት ያደረገው ቢሆንም ምንም ያልተሰማው ለመምሰል ቀጭን ከንፈሮቹን ወደ ግራና ቀኝ እየለጠጠ በመፅሀፉ እንድትገባ ምልክት ሰጣት። ከፊቱ ቀደም ብላ ቆመች። ጎረምሳው አብሯት ሊያልፍ ሞከረ። ሀሰን መፅሀፉ ላይ እንዳፈጠጠ መሀከላቸው ገባ። ጎረምሳው ትልቅ አሻጥር እንደተሰራበት ሁሉ በሸቀ። በቁሟ መቀመጫዋን መተሻሸት በመከልከሉ በግፍ የተገረፈ ያህል ተማረረ።

.

ከጎን ያለው ሰልፍ ላይ ያሉት ሰዎች ሸገር ባስ ውስጥ ለመግባት ይራወጣሉ። ሰልፈኞች ተራ አስከባሪዎች ላይ ይጮኻሉ። ተራ አስከባሪዎች ደግሞ ያለ ሰልፋቸው ጣልቃ የሚገቡት የሰልፍ ቀማኛ ሌቦችን ይገፈትራሉ። ሜክሲኮ አሁንም ከግርግሯ አልቦዘነችም። የመንገድ ዳር ነጋዴዎቹ ተመልሰው ሸያጫቸውን አጧጡፈዋል። ለብሰው ያልለበሱ ብዙ ሴቶች ገላ ላይ የወንዶች አይን ይንከራተታል። በአይኖቻቸው ይዳብሷቸዋል። ያሻሿቸዋል። የጭናቸውን ክፋይ ያንፈራግጡባቸዋል። ሜክሲኮ ላይ ካለው አንድ ኮሌጅ ወጥተው ሲዞሩ አምሽተው ሰልፉን የሚቀላቀሉት ሴቶች ከትምህርት ሳይሆን ከራቁት ጭፈራ ቤት የሚመለሱ ይመስላሉ። ወንዱን ሁሉ በተራቆተ ገላቸው ድፈሯቸው ድፈሯቸው ያሰኛሉ። አንድ ወንድ ከሰልፉ ተንደርድሮ ወጥቶ ገላዋን አራቁታ ስሜቱን የቀሰቀሰችበትን ሴት ቢደፍር ምን ይደረጋል? ይታሰራል። እሷስ? እያለቀሰች "ወጥተን መግባት አልቻልንም፤ እኔስ አንዴ ተደፈርኩ ለሌሎች እህቶቼ መፍትሔ ይፈለግ!" ብላ በቴሌቭዥን ታወራለች። ጎረቤቶች ምናምን ደግሞ ሲጠየቁ "መንግስት ሴት የደፈረን መግደል አለበት። ሴት እኮ እህት ፣ እናት ፣ ሚስት ናት።" ይላሉ። ይሄ ሁሉ ኮተታቸው ለሀሰን ምንም ነው። ምንም! ልጁ ልጅቷን ለመድፈሩ ገላዋን ገላልጣ ፣ ጡቶቿን አሳይታ ፣ ጭኖቿን ከፋፍታ በቻለችው ሁሉ አስተዋፅዖ ያበረከተች ናትና ቅጣቱን እኩል መካፈል አለባቸው ብሎ ያምናል። አካል ብቻ አይደለም የሚደፈረው! ከአካል በላይ የስነ ልቦና መደፈር ያማል። ልጁ ልጅቷን ሲደፍር አካሏን ነው የደፈረው። እሷ ግን እንዲደፍራት ያነሳሳችው ስነ ልቦናውን ደፍራው ነው። ጨዋነቱን በተራቆተ ገላዋ ካባራ ዝናብ ጣራ ላይ እንደተረፈ ውሀ ፤ ጠብ ጠብ እያለ ከስሩ ያለውን ድንጋይ እንደሚበሳው የልቡን ንፅህና በተጋለጠ ገላዋ የስሜት እንፋሎት አሳድፋው! "የስነ ልቦና ቀውስ ደረሰብኝ" ትል ይሆናል። የወንድ አይን መብት የለውም? ወይስ የሴት ገላ መብት ይበልጣል?

.

የታክሲ ሰልፉ እየተገመሰ ፣ እየተገመሰ ሄደ። ልጅቷ የመጀመሪያዋ ሰልፈኛ ሆነች። ተራ አስከባሪው

ከሰልፉ ወደ ፊት ራቅ ብሎ የቆመ ታክሲ አጠገብ ቆሞ "አንድ ሰው!" አለ። ልጅቷ ስላስቀደማት እንደማፈር ብላ ሀሰንን እንዲገባ ጠየቀችው። ትቷት ቢገባ ለጎረምሳው ነፃ የማሸት እድል መስጠት እንደሚሆን አሰበና እንድትቀድም ጋበዛት። ሲጀመርም ለወጉ ጠየቀችው እንጂ ሰልፉ ላይ የመቅረት ፍላጎት የላትም። ትንሽ ተግደርድራ ወደ ታክሲው ሄደች። የለበሰችው ቀሚስ ጎረምሳውን ላደረገው ድርጊት የሚያነሳሳ አይነት አልነበረም። ከላይም ገላዋ አልተጋለጠም። ወደ ታክሲው ስትሄድ ሀሰን መፅሀፉን እያየ ተከዘ። ፍርሀቷ አመመው። የጎረምሳው አይኖች ተጉረጠረጡ።
"አስቀድመኝ ብላህ ነው?"
"አይ ....... ያው ሰልፉችን ተምታታ መሰለኝ።"
"ማለት?"
"በቃ ......... ያው እንደመግደርደር ነዋ! አብራችሁ ነበራችሁ እንዴ?" እንዳልነበሩ ያላወቀ ይመስል
"አይ! አይደለንም።"
ልጅቷ የገባችበት ታክሲ ውስጥ ሌሎች ሰዎች በትርፍ ሊገቡ ሲሉ ጎረምሳው ጮኸ።
"እዚህ ጋር ሰው አይደለን እንዴ የቆምነው! አስወጣቸው!" እያለ ወደ ታክሲው ተራመደ። ሀሰን የሰራው ስራ ሁሉ ገደል ሲገባ ተሰማው። ጎረምሳው ልጅቷን የማሰቃየት ሌላ እድል ያገኘ መሰለው። ጎረምሳው ታክሲ ውስጥ ሲገባ ተራ አስከባሪው "ሶስታችሁ ኑ!" አለ። ሀሰንን ጨምሮ ሌሎች ሰልፍ ላይ የነበሩ ሶስት ሰዎች ወደ ታክሲዋ ገቡ። ጎረምሳው የመጀመሪያው ወንበር ላይ ትርፍ ሆኖ ተቀምጧል። ሀሰን ደግሞ የመኪናው ባትሪ ላይ። ከጎረምሳው ጋር ፊት ለፊት ተያዩና አንገቱን ሰበረ። ጎረምሳው እየተዟዟረ ልጅቷን ይፈልጋታል። አታመልጠኝም የሚል ይመስላል። የታክሲው የውስጥ መብራት ስላልበራ ጨለማ ነው። ፊልጎ አጣት መሰል ፊቱን ወደ ሀሰን መለሰ።
"መፅሀፉ ስለቺኮች ነው አይደል?"
"አይደለም!"
"ስለ ቡና ቤት ሴቶች መስሎኝ እኮ ነው።"
"አይ እንደዛ እንኳን አይደለም።"
ጎረምሳው መፅሀፉን ተቀበለውና ዙሪያውን ካሰረው ቦርሳ ውስጥ ጭንቅላት ላይ የሚታሰር ባትሪ አውጥቶ ካሰረ በኋላ አበራው። መፅሀፉን ገለጥ ገለጥ እያደረገ አነበበ። ሀሰን የልጅቷ ፍርሀት ፣ አይኗን የሞላው እንባ ፣ የሚንቀጠቀጡ ከንፈሮቿ በአይኑ ውል እያሉበት የእልህ እንባ አይኑን ሞላው። እንዲህ በአደባባይ ክብሯን ስትገፈፍ ጎረምሳውን ሰማንያ መግረፍ አለመቻሉ አመመው። ጎረምሳውን ትክ ብሎ ተመለከተው። ንግግሩ አይወለካከፍም ........ ሲራመድ ያየው ጊዜም ጥቂት እንኳ አልተወጋገደም። በልክ ነው የጠጣው .......... በልክ ነው የሰከረው ......... ከስራ ሲመለስ በአግባቡ ጠጥቶ ነው የልጅቷን መቀመጫ ያሸው ........ ክብሯን የገፈፈው ........ አይኖቿን በእንባ የሞላው ........ ደህንነት እንዳይሰማት ያደረገው። በልኩ ነው የደፈራት! በልኩ!
.
ጎረምሳው ግንባሩ ላይ ያሰረውን መብራት አጥፍቶ ወደ ቦርሳው ከተተው። መፅሀፉን እየመለሰለት "ይገርምሀል እኔ ማንበብ የምወደው ማታ ነው። እንደውም አንድ መፅሀፍ በአንድ ለሊት የምጨርስበት

ጊዜ አለ።" አለው። መልስ ሊሰጠው ስላልፈለገ የግዱን ፈገግ አለለት። ታክሲው ልደታ ጋር ሲደርስ ጎረምሳው "ሰላሜ! እሷን አስገባት!" ብሎ ጮኸ። የጋቢናው በር ተከፍቶ በቁሟ የተደፈረችው ልጅ ወርዳ ሰው አስወረደችና ወደ ጋቢናው ተመለሰች። ጎረምሳው የጠራት ልጅ ሰላም ከሚገፋፉት ሰዎች ተነጥላ ልጅቷን ተከትላ ወደ ጋቢናው ገባች። ሰላም ቆንጆ ትመስላለች። ጎረምሳው አንገቱን ወደ ጋቢና አስግጎ ያወራታል።
መኪናው ኮካ ጋር ባለው የመኪና ጭንቅንቅ ታስሮ ቆመ። የታክሲው ረዳት ለሚቀበለው ሶስት ብር ምላሽ የሚሆነውን ሀያአምስት ሳንቲም አይመልስም። ማንም መልስልኝ አይለውም። ሁሉም በመዘረፉ ተስማምቷል። ባይስማማውም ስድብና ማንቋሸሹን ላለማዳመጥ ሲል በግድ ይስማማዋል። ረዳቱ የመንገዱ መቆላለፍ ብስጭት እያደረገው "ኤጭ! አሁን መንገድ ሰራን ይላሉ ኢያፍሩም! ሌቦች!" አለ። ሀሰን ውስጡ ቅጥል ብሎ ረዳቱን ይመለከተዋል። በልቡ " ላንተ አይነቱ ሌባ መንገድ መስራታቸው በራሱ እጅግ ሲበዛ ነው!" ይላል። ሌቦች ማለቱ አብግኖታል። "እሱ እንኳ በዚህች ሚጢጢ ስራው እና በአመዳም ፊቱ ከሰው ሀያአምስት ሳንቲም እየዘረፈ ስልጣን ያላቸው ሙሉውን የህዝብ ሀብት ቢወስዱ ምኑ ላይ ነው ጥፋቱ?" ሲል ራሱን ይጠይቃል። መስረቃቸው ጥፋት መሆኑ ባይካድም የዚህ አይነቱ ሌባ ግን ሊዳኛቸው አይገባም። ሁሌም በሄደበት እራሳቸው ሌባ ሆነው መንግስትን የሚሳደቡ ሌቦች ይቀፉታል። ህዝብ ነቅዞ መንግስት የማይነቅዝበት ምክንያት አይታየውም።
ታክሲው ጦርሀይሎች ታክሲ ተራ ሲደርስ መፅሀፉን ከጎረምሳው ተቀበለው። ሰላምና ሚስኪኗ ልጅ ከጋቢና ወረዱ። ሀሰን አይኖቹን ሚስኪኗ ልጅ በሄደችበት አቅጣጫ ልኮ ፈዘዘ። የሴቶች መብት ለይስሙላ "ሴት ማለት እህት ፣ እናት ፣ልጅ ናት!" በሚል ተራ ማስታወቂያ በሚፎገርበት ሀገር የህብረተሰቡን ስነ ልቦና የሚቆጣጠሩ የአተላ ማስታወቂያዎች ከቀን እስከ ማታ እንደ አባይ ያለማቋረጥ መጉረፋቸው አመመው። በልክ የሰከሩ ....... በልክ ሲደፍሩ ........ ብስጭት አለ።
ውስጡን እልህ ሞላው። የዛሬዋን ሚስኪን ክብሯ ሲገፈፍ ቢያንስ ገላገላት ....... ነገስ ሲመሽ በደህና ወደ ቤቷ መመለስ ላትችል ነው? ....... ሲያገባ ሚስቱንም እንዲህ ሊያሹበት? ......... ክብሯን ሊገፉበት? ......... ልቡ ውስጥ ከትውልዱ ተስፋ ሲቆርጥ ተሰማው። ከአይኖቹ የእንባ ዘለላዎች ተሽቀዳደሙ። ነገስ?
.
ተፈፀመ።